# የቅንጅት ፓርቲ አንደኛ ጠቅላላ ጉባኤ ተካፋዮች

## የጋራ መግለጫ

መስከረም 14/1998 ዓ.ም ውኽደቱን የፈጸመው ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ከሰኔ 14 እስከ ሰኔ 15/2000 ዓ.ም ድረስ 1ኛ ጠቅላላ ጉባኤውን በአዲስ አበባ አድርጓል፡፡

በዚህ ጉባኤ ላይ ፓርቲው ባለፈው ያከናወናቸውንና ወደፊትም ሊያከናውን ያቀደውን መርምሮ አጽድቋል፡፡ በወደፊቱ ጉዞ ላይ ሊያጋጥሙ ይችላሉ የሚላቸውን ችግሮችም አንድ በአንድ በመዳሰስ ለእንቅስቃሴው አመቺ የሆኑ ስልቶችን በመቀየስ የሚከተለውን የጋራ አቋም አውጥቷል፡፡

ፓርቲው በአሁኑ ጊዜ ያጋጠሙትን ችግሮች ለማሸነፍና ቅንጅትንም ለማዳን በአቶ ኃይሉ ሻውል የሚመራው የሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴ ያደረገውን ከፍተኛ ትግልና ያስገኘውን ውጤት ጠቅላላ ጉባኤው ከልብ ያደንቃል፣ በተለይም አላግባብ ለሌላ የተሰጠውን የቅንጅትን ስምና ዓርማ ለማስመለስ በፍርድ ቤት ክስ በማቅረብና በሕግ መንገድ የፓርቲውን መብት ለማስከበር በፍርድ ቤት በኩል የተጀመረው ክርክር ቀጥሎ ፓርቲው ያለውን ሥርዓት ተጠቅሞ መብቱን ለማስከበር ከሚወስደው እርምጃ አንፃር የሚደገፍ ነው፣ ስለሆነም ይኸው ተጠናክሮ እንዲቀጥል በማሳሰብ የሚከተለውን ተጨማሪ መመሪያ ጠቅላላ ጉባኤው ሰጥቷል፡፡

1. ጉባኤው ስለ ፓርቲው ስምና የምርጫ ምልክት ባደረገው ውይይትና በሰጠው መመሪያ አሁን በፍርድ ቤት የተጀመረው ክስ ውሳኔ ውጤት እንዳገኘ የሥራ አስፈጻሚው የፓርቲውን ስምና የምርጫ ምልክቱን ሰይሞ ለበታች አካላትና ለሕዝብ በይፋ እንዲያስታውቅ ሙሉ ውክልና ሰጥቷል፡፡
2. የማደራጀት አቅምና የገንዘብ ሁኔታ እስከፈቀደ የፓርቲው ቅርንጫፎችን እስከ ወረዳ ድረስ በቅደም ተከተል ማቋቋሙ በትጋት እንዲቀጥል ሆኖ የፓርቲውን መዋቅርና እንቅስቃሴ በሕዝብ መካከል እንዲደርስ በማድረግ ረገድ በየደረጃ የምንገኘው የፓርቲው አካላትና አመራሮችም የተጠየቀውን መስዋዕትነት ለመክፈል መዘጋጀታችንን እናረጋግጣለን፡፡

በአገራችን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሕዝብ ተደራጅቶ ዴሞክራሲያዊ መብቱን ለማስከበር የሚያደርገው እንቅስቃሴ አዲስ የዴሞክራሲ ባህል እንዲሰፍን ለማድረግ

3. በመሆኑ ከፍተኛ መስዋዕትነትን የሚጠይቅ እንደመሆኑ ይህንኑ የትግል መንገድ ተከትሎ በፅናት መቆም አማራጭ የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ለዚህ ዓላማም መሳካት የሚያስፈልገውን መስዋዕትነት ለመክፈልና ትግሉን ከዳር ለማድረስ በትጋት ለመሥራት ደግመን ቃል እንገባለን፡፡
4. ቅንጅትን ለመበታተን በውጭ ኃይሎች ከሚሸረበው ደባ ተያያዥነት ያላቸው ወገኖች በአመራራችን መካከል ሠርገው በመግባት ያደረሱትን ጥፋት ተገንዝበናል፡፡ ከነዚህ አፍራሽ ኃይሎች አንፃር በልበ ሙሉነት ለፓርቲው ደኅንነት ቆመው ጥፋቱን በመከላከል ፓርቲው ሕልውና እንዲጠበቅ ያደረጉትን የፓርቲውን አመራርና አባላት ከልብ እናደንቃለን፡፡ አሁንም የተመረጡት የፓርቲው የላዕላይ ምክር ቤትና የሥራ አስፈጻሚ አባላት የፓርቲውን ሕልውና በማስከበር የአባላትን አንድነት የበለጠ እንዲጠናከር በማድረግ በኩል ተግተውና ጠንክረው እንዲሠሩ ከአደራ ጭምር ሙሉ ኃላፊነቱን ሠጥተናል፡፡
5. የቅንጅትን ፓርቲ የመሠረቱት አራቱ ፓርቲዎች ውህደት ካካሄዱ በኂላ የየፓርቲዎቹ ንብረቶች የቅንጅት ንብረት ሆነዋል፤ እንዲሁም በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በቅንጅት ስም ከሕዝብ የተሰበሰበ ገንዘብ በየቦታው እንዳለም ተገንዝበናል፤ ስለዚህ እነዚህን ሁሉ የፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ ተከታትሎ ወደ ፓርቲው እንዲያስገባ አደራ ጭምር ኃላፊነት ሰጥተናል፡፡
6. በአገራችን የሥልጣን ሽግግሩ ከምርጫ ሣጥን በሚገኝ የሕዝብ ምርጫና ፈቃደኝነት ላይ እንዲሆን በፓርቲያችን ግንባር ቀደም መሪነት የሚደረገው ሠላማዊ ትግል በስፋትና በጥራት እንዲቀጥል ከመቸውም የበለጠ ጠንክረን መሥራት እንዳለብን እንገነዘባለን፡፡ በተለይም ፓርቲያችንን ለማዳከምና ለማፈራረስ ከውስጥም ሆነ ከውጭ የሚነሱትን ፀረ-ሕዝብና ፀረ-ዴሞክራሲ ኃይሎች በቆጥራነት ለመታገልና ሠላማዊ ትግሉን ከዳር ለማድረስ የምንጠየቀውን መስዋዕትነት ሁሉ ያለገደብ ለመክፈል መዘጋጀታችንን ደግመን እናረጋግጣለን፡፡

የኢትዮጵያ አንድነት ክብርና ጥቅም
በመስዋዕትነታችን ይከበራል!!
እናሸንፋለን!!